# ኣውራ ዶሮ



ያረጀ ኣውራ ዶሮ
ሲጮኽ በማለዳ
ደግሞም ሲንጎራደድ
ግራ-ቀኝ ወልጋዳ

በወጣትነቱ፣ ሜዳው፣ ቁልቁለቱ፣
ኣወይ ጉልምስና
ሲወጣና ሲወርድ፣ ተራራው፣ ዳገቱ፣
የዛሬን ኣያድርገው፣ መጣ ሽምግልና
ክንፉን ሲያርገበግብ፣ ሲቦርቅ ነበረ
እርጅና መጣና ይኸም ሁሉ ቀረ።

ኣፈር ጭሮ-ግሮ
ጥራ-ጥሬ ለቅሞ
ያረጀ ኣውራ ዶሮ
ሥራ መች ለግሞ!

ኣይ ኑሮ ዘልዛላ - ሁሌ ተወጣጥሮ
መቸምውኑም ኣይሞላ - የና ኣውራ ዶሮ
ደሙን ሲያርከፈክፍ በስንቱ ጦር ሜዳ
ዛሬ ዕድሜ ጥሎት ወረደበት ዕዳ
ይኸ ኣይደል? ወይ ዕድል...
ኣጨማልቆ እንጂ፣ እንደ ሠራ ኣይገድል!



በውድቅት ማለዳ
ኩኩሉ - ኣልነጋም
መኮትኮቻው ድልዱም
ጥፍሩም ኣይዋጋም

ጣራና ግድግዳው፣ ምሰሶ ማገሩ፣
ጀግናው ኣውራ ዶሮ
ዝሆንና ኣውራሪስ፣ ኣንበሳና ነብሩ፣
ጋሻና ጦር ይዞ፣ ጎራዴ ተማዝዞ
ሲያድን የነበረ ጉማሬና ኣዞ...
ዛሬ ሁለመናው፣ ዕድሉ ተሰብሮ
ዓይኑ ሁሉ ፈዝዞ፣ ኣንደበቱ ታስሮ...

ቢታገስ ይሻሏል
ሌሊቱ እስኪነጋ
ቁርጥማት ሲበላው
ደም-ስሩ እየረጋ...
ኣውራ ዶሮ ኣይወድም
ኣረጀህ ሲሉት

እምብርክክ እስኪሄድ
እስኪንኮታኮት

በወጣትነቱ ደረቱን ለጦር
እግሩን ለጠጠር
በኣየር፣ በምድር፣ በባሕር ባቡር
ሲዋጋ፣ ሲደማ፣ ሲቆስል ነበር
ዛሬ ተስኖታል ሽንቱን መቋጠር!

ኣርጅቷል፣ ኣብቅቷል
ጥፍር፣ ጥርሱ ወልቆ
ግን እጁን ኣይሰጥም
ሳይሞት መሬት ወድቆ

**ገ/ኢ. ጐርፉ።**

